// 
# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምፅ

Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

efdpu@aol.com www. Finote.org

**ፕሮግራም**፡- ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 13 ሜትር ባንድ

**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band.

## <u>ዜና ዘገባ</u>

**ህዳር 1 ቀን 2005 ዓ.ም**

**የወያኔ ባለስልጣናት ያደረጉት ምስጢራዊ ስብሰባ እና ንትርክ ለህዝብ እንዳይተላለፍ ተደረገ፤**

**የትግራይ ህዝብ በነባር የህወሀት ባለስልጣናት ፍዳውን እያየ መሆኑ ተጋለጠ፤**

**የኦህዴድ እና የወያኔ ስራ አስፈጻሚ አባሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ሰሞኑን ከእይታ መሰወሩ እያነጋገረ ነው ፤**

**ቤተክርስቲያንዋ ምንግዜም የአንዲት ኢትዮጵያ ሀብት ናት ሲል ሲኖዶሱ የወያኔ ካድሬዎችን አጣጣለ፤**

እርስ በርስ ባለመተማመን እየታመሱ የሚገኙት የወያኔ ቡድን ባለስልጣናት ከመቼውም ግዜ በላይ ግራ ተጋብተው በየቀኑ ድንገተኛና አስቸኩዋይ በሚል በስብሰባ ተወጥረው እንደሚገኙ ከደረሰን ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

እርስ በርስ እየተሸኮቱ የሚገኙት የወያኔ ባለስልጣናት አንዱን ሲቁዋጥሩ ሌላው እየተፈታባቸው መላው ጠዋት የወሰኑትን እንደገና ከሰዓት በሁዋላ እየሻሩ. ባለበት በአሁኑ ግዜ እራሳችንን እናጽዳ የሚል አዲስ ዘመቻ መጀመራቸውም ታውቆዋል::

ቅዳሜ ጥቅምት 24 ቀን 2005 ዓ.ም የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ድንገተኛ ና አስቸኩዋይ ስብሰባ አደረገ የተባለ ቢሆንም ስለዋሉበት ስብሰባ አንዳችም ሳይገለፅ በመቆየቱ የመካከለኛ ውና የታችኛው ካድሬ በጉዳዩ ግራ ተጋብቶ ሲታመስ እንደነበረም የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል::

አስቸኩዋዩ የወያኔ ስራ አስፈጻሚ ስብሰባ ከመደረጉ አስቀድሞ በነበሩት ቀናት ውስጥ በተከታታይ እራሳችንን እናጽዳ በሚል በፓርላማ ህንጻ መሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ በዝግ ሲነታረኩና ሲወዛገቡ የሰነበቱ መሆኑን የጠቆሙት እነዚሁ ውስጥ አዋቂ የድርጅቱ አባሎች የንትርኩን

ሂደት ለህዝብ በመገናኛ ብዙሀኖች እንደወረደ ይፋ እንዲደረግ ብለው ውሳኔ የተላለፈና ማስታወቂያ የተነገረ ቢሆንም በማግስቱ የተባለው ቀርቶ ሊታፈን እንደቻለም እነዚሁ ምንጮች አጋልጠዋል፡፡

የወያኔ ቡድን ሰሞኑን በአራት ኪሎ በሚገኘው በፓርላማው የቋሚ ኮሚቴ መሰበሰቢያ አዳራሽ ውስጥ ባልተለመደና እስከ ዛሬ ባልታየ ሁኔታ እርስ በርስ ሂስ እና ግለሂስ መሰል ኑዛዜ ሲያደርጉ ከመሰንበታቸውም በተጨማሪ የውይይቱ መንፈስና ውሳኔ በመገናኛ ብዙሀን ይፋ ይደረግ ተብሎ ውሳኔ ተሰጥቶት የነበረ ቢሆንም በበረከት ስምኦንና በጥቂት የህወሀት ሰዎች በኩል ታግዶና ሳንሱር ተደርጎ ከቀናት በሁዋላ መቅረቡን ተከትሎ በወያኔ ቡድን ውስጥ ችግር መኖሩን የሚያሳይ ነው ሲል የእነዚሁ ውስጥ አዋቂ የድርጅቱ አባሎች ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

ማዕከላዊነት እየተዳከመና በአጭር ግዜ ውስጥ የወያኔ ቡድን ሊሰነጠቅ ይችላል ተብሎ ከፍተኛ ስጋት ውስጥ በወደቀበት በዚህ ግዜ ዝግ ስብሰባና ንትርክ ባደረጉበት ወቅት ከፍተኛና ነባር የወያኔ ባለስልጣናት ከወጣቶቹ አፍለኛ ባለስልጣናት ጋር በሀሳብ ልዩነት ፈጥረው እርስ በርስ ሲነታረኩ የሰነበቱ ሲሆን በተለይ የህወሀቱ አባይ ጸሐዬ እስከ ዛሬ በህዝብ እና በሀገር ላይ ሲፈጽሙ የነበረውን አዳፋ ታሪክ ለመደበቅ እና ከተጠያቂነት ለማምለጥ በድፍኑ ሽፋፍኖ ለማለፍ ሙከራ ሲያደርግ የነበረ ቢሆንም ወጣቶቹ የነበረውን የተሳሳተ አሰራር በግልጽ እያስቀመጡ ሲተችዋቸው እንደነበር ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

የነባር በረሀ አመጣሽ ባለስልጣናት እና አፍለኛ ወጣት በለስልጣናትን ለማግባባት መሀል ሰፋሪ ሆኖ ሲያንቀሳቅስ የነበረው ምርኮኛው የኦህዴዱ አባዱላ ገመዳ ስራቸውን በአግባቡ የማይሰሩ.....በዘመድ አዝማድ የተተበተበ ኪራይ ሰብሳቢነት ያሳዩ......የተሰጣቸውን ስራ በአግባቡ የማይወጡ...... በመጀመሪያ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶዋቸው ለውጥ ካላሳዩ ከስልጣናቸው ከመነሳታቸውም በተጨማሪ እንደ አስፈላጊነቱ ሊከሰሱ እንደሚችል በስብሰባው ላይ መግለጹንም ምንጮቹ ገልፀዋል፡፡

ለ21 ዓመታት በህዝብ ጫንቃ ላይ ሲያናጥሩ የኖሩትና በህዝብ እና በሀገር ላይ ደባ ሲፈጽሙ የነበሩትን እነዚሁ የወያኔ ቱባ ባለስልጣናት ከተጠያቂነት ለማዳን ሲባል አዲስ ዘመቻ የጀመሩ ሲሆን እግረ መንገዳቸውን የህዝብ ድጋፍ ለማሰባሰብ እንዲረዳቸው ያደረጉት መሆኑንም ምንጮቹ አክለው ገልፀዋል፡፡

የህዝብ ድጋፍ ለማግኘት ከተፈለገ ጥፋት ያጠፋው ባለስልጣን ጥፋቱ ለህዝብ ይፋ ተደርጎ ቅጣት ሲጣልበት መሆኑን ሲሞግቱ የሰነበቱት አፍለኛ ባለስልጣናት በአሁኑ ሰዓት የሕዝቡ ድጋፍ ካልታከለ በስተቀር ድርጅቱ ከፍተኛ አደጋ ላይ ሊወድቅ እንደሚችልም መናገራቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

ቀድሞ የነበረው የእርስ በርስ ሽኩቻና ንትርክ እልባት ሳያገኝ በእንጥልጥል ላይ እንዳለ ሆኖ አሁን ደግሞ ግልጽነት..... ተጠያቂነት....ስልጣንን አላግባብ መጠቀም.....በሚሉ ጉዳዮች ላይ ውይይት ሲያደርጉ የነበረ ቢሆንም ነባሮቹ የወያኔ ባለስልጣናት እስከ ዛሬ የፈጸሙትን በደል የሚያጋልጥባቸው በመሆኑ ሊሰራጭ የነበረው ሙሉ ፕሮግራም ተቆራርጦ እንዲቀርብ መደረጉንና ይህንኑ ተከትሎ ብዙ ወጣት ባለስልጣናት ክፉኛ መቆጣታቸውን ምንጮቹ አጋልጠዋል፡፡

በሌላ ዜና ህወሀት ከተመሰረተና ስልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ እስከ ዛሬ ያልተደረገ ህዝባዊ ስብሰባ በትግራይ ሁሉም ከተሞች በግዴታና በድለላ መደረጉን ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አጋለጠ፡፡

በመቀሌ ከተማ ሰማዕታት አዳራሽ ተብሎ በሚጠራው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ውስጥ የህወሀት ከፍተኛ አመራሮች ብቻ ሲመክሩ የሰነበተ ሲሆን ይህንኑ ምስጢራዊ ስብሰባ ተግባራዊ ለማድረግ በመላ የትግራይ ክልል ከተሞች ህዝቡን እያስገደዱ..... እያስፈራሩና... በገንዘብ እያታለሉ ህዝባዊ ስብሰባ ሲያደርጉ መሰንበታቸው ታውቆዋል፡፡

በመላ ትግራይ ከገጠር እስከ ከተማ ነዋሪ የሆኑ እድሜያቸው ከ15 ዓመት እስከ 65 ዓመት ድረስ ያሉትን ዜጎች በግዴታና የውሎ አበል በመክፈል ስብሰባ የተደረገ ሲሆን ዋነኛው ዓላማው ህወሀትን ከዚህ ቀደም ከነበረው በላይ በሀገሪቱ የበላይ ሆኖ እንዲቀጥል ለማድረግ እንደሆነም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አብራርቶዋል፡፡

ስብሰባውን በተለያዩ ቦታዎች ተከፋፍለው ሲመሩት የነበሩት ነባር የበረሀ አመጣሽ ሽማግሌ የህወሀት ባለስልጣናት ሲሆኑ እነሱም ሴቶቹን...... ወንዶቹን .......ወጣቶቹን እና ባለሀብቶቹን በመለያየት እና በመከፋፈል የትግራይ ህዝብ ከተቀረው የሀገሪቱ ወንድሙ ጋር በሰላምና በፍቅር እንዳይኖር ቅስቀሳ ሲያደርጉ መሰንበታቸው ታውቆዋል፡፡

ከዚህ ቀደም በተለያዩ ግዜያት የትግራይን ጭቁን ህዝብ ከተቀረው ወገኑ ጋር ለማጋጨት ሞክረው ያልተሳካላቸው የወያኔ እድሜ ጠገብ ሽማግሌ ባለስልጣናት ጡረታ በመውጫቸው ላይ አሁን እንደ አዲስ ህዝቡን ሊያጋጩ ቅስቀሳ መጀመራቸውን ህዝቡ መቃወሙንም ከስፍራው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል፡፡

የህዝብ ድጋፍ ያጡት እና ዙሪያው ገደል የሆነባቸው የወያኔ በተለይ የህወሀት ነባር ባለስልጣናት እስከ ዛሬ ለሰሩት ግፍ እና ለፈጸሙት በደል ንስሀ ገብተው ህዝቡን ይቅርታ ከመጠየቅ ይልቅ እርስ በርስ እንዲከፋፈልና ችግር ውስጥ እንዲዘፈቅ ለማድረግ በትግራይ ውስጥ እየተዘዋወሩ ቅስቀሳ ሲያደርጉ መሰንበታቸው አሳፋሪና አሳዛኝ ነው ሲል የትግራይ ህዝብ በብስጭት ሲናገር ተደምጦዋል፡፡

በተያያዘ ዜና በወያኔ ቡድን ውስጥ ትርምሱና ሽኩቻው እየሰፋና እያደገ በመጣበት በአሁኑ ወቅት የዚሁ ቡድን ዋነኛ ሰው የሆነው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ  ኩማ ደመቅሳ ሰሞኑን ከመድረክ መጥፋቱ በወያኔ ካድሬዎች ዘንድ መነጋገሪያ መሆኑ ታወቀ፡፡

የኦህዴድ እና የወያኔ ስራ አስፈጻሚ አባሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ ሰሞኑን ዋና ዋና ከተባሉ  ስብሰባዎች ላይ ካለመገኘቱም በተጨማሪ በተለይ የስራ አስፈጻሚው ስብሰባ ላይ አለመታየቱ ግለሰቡ ምን ሆነ የሚል ጥያቄ በካድሬዎቹ ዘንድ ጥርጣሬን የጫረ ጥያቄ እያነሱ መሆኑም ታውቆዋል፡፡

ለወያኔው መሪ ለነበረው ለሙዋቹ መለስ ዜናዊ ከፍተኛ ቅርበት የነበረውና ሁሉን ትዕዛዝ እና ስድብ ውጦ በማስቀረቱ  ስፖንጅ የሚል ቅጽል ስም  የተሰጠው የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ ኩማ

ደመቅሳ ከተማዋ 125ኛ ዓመቱዋን ለማክበር ደፋ ቀና በምትልበት በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ ካለመገኘቱም በተጨማሪ በተለይ የስራ አስፈጻሚው ስብሰባ ላይ አለመታየቱ የብዙዎቹ አፍለኛ ወጣት ካድሬዎች መነጋገሪያ ሆኖ መሰንበቱ ታውቆዋል::

በቅርቡ የወያኔን ስርዓት ከድተው ከፈረጠጡት ባለስልጣናት መሀከል አንዱ የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ከፍያለው አዘዘ የተባለው ግለሰብ የሚገኝበት ሲሆን ምናልባት ከዚሁ ግለሰብ ጋር በተያያዘ ኩማ ደመቅሳ ጥያቄ ምልክት ውስጥ ሳይገባ እንዳልቀረም ግምታቸውን የሚሰነዝሩ የወያኔ ካድሬዎች ብዙዎች መሆናቸው እየተነገረ ቢሆንም ሰውዬው ከቅርብ ግዜ ወዲህ ለከፋ የጤና መታወክ ስለተዳረገ ለህክምና ወደ ውጭ ሀገር ሳይወጣ እንዳልቀረም ግምታቸውንም የሚሰነዝሩ ብዙዎች ናቸው::

በአሁኑ ሰዓት የኩማን ቦታ ተክቶ እየሰራ ያለው በቅርብ ግዜ ከባህር ዳር ተዛውሮ የመጣው የብአዴኑ አባተ ስጦታው የተባለው ባለስልጣን ሲሆን በሁሉም ቦታ ላይ እሱ እና እሱ ብቻ እየተገኘ ውሳኔ እያስተላለፈ እንደሚገኝም ከምንጮቹ ጥቆማ ለመረዳት ተችሎዋል::

ወያኔ አዲስ ብሎ በቅርቡ ከሚፈጽማቸው እርምጃዎች አንዱ የሹም ሽር ሲሆን በተለይ በአዲስ አበባና በድሬዳዋ ሹማምንቶች ላይ የከረረ እርምጃ እንደሚወስድ እየተጠበቀ ይገኛል ::

በድሬዳዋ እና በአዲስ አበባ ከፍተኛ ባለስልጣናት ላይ የተጀመረው የምንጠራ ዘመቻ እየሰፋ የመጣ ሲሆን በተለይ የድሬዳዋ ከተማ የቢሮ ኃላፊዎች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት እንደሚባረሩና በምትካቸው ሌላ ያልጠገቡ ካድሬዎች ሊሾሙ በዝግጅት ላይ መሆናቸው ታውቆዋል::

በተለይ ከአንድ ዓመት በፊት ጀምሮ የራሱ ተከታይ ናቸው የተባሉ የበረከት ስምኦን ጀሌ ወጣት አዲሶቹ አፍለኛ ካድሬዎች የድሬዳዋና የአዲስ አበባ ከተማን ሙሉ ለሙሉ እንዲቆጣጠሩ ለማድረግ እየተሰራ ሲሆን እነ ኩማም በመተካካት ስም ከስልጣናቸው በቅርቡ ሊወገዱ ይችላል ተብሎዋል::

በአሁኑ ሰዓት በድሬዳዋ ከተማ የከተማዋ ሹማምንቶች በፌዴራል ከፍተኛ ባለስልጣናት መሪነት ስብሰባ መሰል ግምገማ እየተደረገ ሲሆን ስብሰባው እንደተጠናቀቀ ሹም ሽረቱ ይፋ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል::

የድሬዳዋ ከተማ የኢህአዴግ ተጠሪ...የደህንነት ኃላፊው.....የህዝብ አደረጃጀት ቢሮ ኃላፊ......ተጠርተው በአዲስ አበባ በአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ውስጥ ከበረከት ስምኦን ፣ከአርከበ እቁባይ፣ ከደመቀ መኮንን ጋር በመሆን በምስጢር ስብሰባ ሲያደርጉ እንደነበረም ከቤተ መንግስት ውስጥ አዋቂ ምንጮች የደረሰን ጥቆማ ገልጾ ይህንኑ ለቀናት የተደረገ ስብሰባ ተከትሎ ከሰኞ ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ በድሬዳዋ የካድሬዎቹ ስብሰባ መሰል ግምገማ መጀመሩንም ለማወቅ ተችሎዋል::

ይህ በእንዲህ እንዳለ በመተካካት ስም ወደ ስልጣን የመጣው ኃይለማርያም ደሳለኝ ቤተ መንግስት ግቢ ውስጥ መለስ ሲኖርበት የነበረውን ቤት ከመረከቡ በፊት ለጽዳት በሚል በፓኪስታን ዜጎች ምስጢራዊ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ሲገጠሙ ሰንብቶ ሰሞኑን ማስረከባቸው ታወቀ::

በብሄራዊ ደህንነት እና መረጃ ባለስልጣኑ በጌታቸው አሰፋ የበላይነት በሚመራው ምስጢራዊ የእድሳት ስራ ተጠናቅቆ ባለፈው ሳምንት እሁድ ዕለት ወደ ቤተ መንግስት የገባ ቢሆንም ነባርና በረሀ አመጣሽ የወያኔ ባለስልጣናት በሰውዬው ላይ እምነት ስለሌላቸው በስውር ካሜራ ገጥመው መቆጣጠር እንደጀመሩም የቤተ መንግስት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ገልፀዋል።

ስውር ካሜራው ሲገጠም ኢትዮጵያዊ ባለሙያዎች እንዳያዩት በሚል ፓኪስታናዊቹን በውጭ ምንዛሪ ከውጭ ሀገር ድረስ ያስመጡት የወያኔ የደህንነት ኃላፊዎች ከ15 ቀናት በላይ በፈጀ ስራ ተጠናቅቆ ኃይለማርያም ወደ ቤተ መንግስት እንዲገባ የተደረገ ቢሆንም በስውር የመሰለያ መሳሪያ መገጠሙን ምንጮቹ አጋልጠዋል።

የጠቅላይ ሚኒስትርነቱን ቦታ ከተሰጠው ከአንድ ወር በላይ ለሆነ ግዜ በአዜብ መስፍን እምቢተኝነት ከቤተ መንግስት ውጭ ሆኖ እየተመላለሰ ሲሰራ የቆየው የደቡቡ ተወላጅ ኃይለማርያም ደሳለኝ እስከ አሁን ድረስ የመለስን ቢሮ እንዳላስረከቡትም ምንጮቹ አጋልጠዋል።

በወያኔ ቡድን ውስጥ የተፈጠረው የቡድንተኝነት ስሜት ወደ መከፋፈል በተቃረበበት ወቅት በመሆኑ በድርጅቱ ውስጥ የእዝ ጠገግ ጠፍቶ ያለበት ስለሆነ ቤተ መንግስቱን ለቅቃ እንድትወጣ ከአንድም ሁለት ሶስት ግዜ በተደጋጋሚ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ተፅፎላት አልለቅም ስትል የቀየችው አዜብ መስፍን ትዕዛዙን ወደ ጎን አድርጋ በነባር የህወሀት ሰዎች እና በአዲሱ ለገሰ ሽምግልና ብቻ ከግቢ ብትወጣም የህዝብ ንብረት የነበሩና ከአጼ ኃይለስላሴ ግዜ ጀምሮ የነበሩ ቅርሶችን ጭና መውሰድዋንም ምንጮቹ አብራርተዋል።

የወያኔ ቡድን በፖለቲካው ከፍተኛ ሽንፈት ከተከናነበ በሁዋላ እና የርስ በርሱ ትርምስ እንዳለ ባለበት በዚህ ግዜ በቤተ ክህነት ውስጥ ጣልቃ በመግባት ጳጳሳቱን ለመከፋፈል ያደረገው ሙከራ መክሸፉ ታወቀ።

በቤተክህነት ሲደረግ የሰነበተው ዓመታዊ የሲኖዶሱ ስብሰባ ባለፈው ሳምንት ውስጥ በንትርክ እና በውዝግብ መጠናቀቁ ታወቀ።ውጭ ሀገር ካለው ሲኖዶስ ጋር የተጀመረው የሰላም ድርድር ግቡን እንዳይመታ የአባ ጳውሎስ ደጋፊ የነበሩና የፓትርክናውን ስልጣን የተመኙ ጳጳሳት ስብሰባውን ሲያውኩ መሰንበታቸው ታውቆዋል።

ከአርባ በላይ በሆኑ ጳጳሳት ለአስር ቀናት ሲደረግ የሰነበተው የሲኖዶሱ ዓመታዊ ስብሰባ ጥቅምት 21 ቀን 2005 ዓም በውዝግብ መጠናቀቁን ከቤተ ክህነት ምንጮች ለማወቅ ተችሎዋል።

ዘመነ ስልጣናቸውን ሙሉ በውዝግብ እና በትርምስ በህልፈተ ህይወት ያጠናቀቁት አባ ጳውሎስ ከሞቱ የመጀመሪያውን ዓመታዊ ጉባዔ ሲያደርግ የሰነበተው ሲኖዶስ እስከ ዛሬ እንዲፈጸሙ ሲወስናቸው የነበሩና በአባ ጳውሎስ እና ደጋፊዎቻቸው ተግባራዊ ሳይደረጉ የነበሩትን ውሳኔ በድጋሚ ሲመረምር የቆየ ቢሆንም አሁንም በቤተ ክህነት ውስጥ ክፍፍል በመፈጠሩ በእንጥልጥል የቀሩ ብዙ ጉዳዮች መኖራቸው ታውቆዋል።

እስከ ዛሬ የቤተክርስቲያንዋ ገንዘብ ገቢና ወጪዋ በአግባቡ ተሰርቶ እንደማይታወቅ ያጋለጠው የሲኖዶሱ ጉባኤ ባለፈው ዓመትም እንደሌላው ግዜ ሁሉ ከ6.5 ሚሊዮን ብር በላይ የት እንደገባ ሳይታወቅ መጥፋቱን ሲኖዶሱ አረጋግጦዋል።

በአሁኑ ሰዓት ቤተ ክህነትን እንደ ፖለቲካ ተቋማት በብሔር እና በሰፈር ለመከፋፈል እየተሰራ መሆኑን ያጋለጠው ሲኖዶሱ ይሄ ተቋዋም የእምነት በመሆኑ ማንም ባለስልጣንም ሆነ ግለሰብ ከእንዲህ ያለ ሰይጣናዊ ድርጊቱ እንዲቆጠብና ጳጳሳትም ይህንን ተልካሻ ተግባር አጥብቀው እንዲኮንኑ ሲኖዶሱ በአንድ ድምጽ ወስኖዋል።

የወያኔ ፓርቲ አባል የሆኑ የአባ ጳውሎስ ቀኝ እጅ የነበሩት ግለሰቦች ሲኖዶሱ በአግባቡ ስብሰባውን እንዳያካሂድ ከፍተኛ እንቅፋት ሲፈጥሩ እንደነበር የጠቆሙት የቤተክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች ግለሰቦቹ ሲኖዶሱን ስብሰባ ለመበጥበጥ እና ጳጳሳቱን ለመከፋፈል ሙከራ ያደረጉ ቢሆንም ሲኖዶሱ ቤተክርስቲያናችን በብሔር ትምክህተኝነት የምትገለጽ ሳትሆን ለኢትዮጵያዊነት ተምሳሌት መሆን የምትችል ብሔራዊ እናት ነች ሲል ባወጣው መግለጫ አቋዋሙን ይፋ አድርጎ እንዳሳፈራቸው ታውቆዋል።

የሲኖዶሱ መግለጫው አያይዞም የቤተክርስቲያናችን ብሔራዊ ተምሳሌት መሆን ያልተመቻቸው እና ከመጠን በላይ መስፋፋትዋ ያስደነገጣቸው አንዳንድ ወገኖች ቤተክርስቲያኒቱን ለመበታተን እና የፖለቲካ ጥገኛ ለማድረግ አቋራጩ መንገድ በብሔር..... በጎጥ..... በዘር እና በመንደር ለመከፋፈል ያደረጉት ሙከራ ከንቱ ከመሆኑም በላይ ቤተክርስቲያንዋ ምንግዜም የአንዲት ኢትዮጵያ ሀብት ናት ብሎዋል።

በስብሰባው ላይ ያለ ስምምነት የተቋዋጨው አንዱና ዋነኛው አጀንዳ 4ኛው ጳጳስ አቡነ መርቆርዮስ ዳግመኛ ወደ ፓትርያርክነታቸው ይመለሱ ወይም አይመለሱ የሚለው የነበረ ሲሆን የሲኖዶሱ ጸሐፊ በሆኑት አቡነ ሕዝቅኤል ግን በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ላይ እንዳሉት እሳቸው በመረጡት ቦታ ወይም ገዳም መቀመጥ እንደሚችሉ ነገር ግን ፐትርክናው እንደማይሰጣቸው መናገራቸው ታውቆዋል።

ለ21 ዓመታት 5ኛ ጳጳስ ስንል ቆይተን ዛሬ ወደ ሁዋላ ተመልሰን 4ኛው ጳጳስ የምንልበት ምክንያት ስለሌለ አዲስ ስድስተኛ ጳጳስ ምርጫ ይደረጋል እንጂ እሳቸው መንበረ ፐትርክናውን አያገኙም ሲሉ ተናግረዋል።

እስከ ዛሬ ለ21 ዓመታት አባ ጳውሎስ እንዳሻቸው ሲፈነጩበት የነበረውን ስልጣን አዲሱን ተሹዋሚ ፓትርያርክ ለመገደብ እና ለመቆጣጠር እንዲያመች በሚል የፓትርያርያኩ ተግባራት እና ስልጣኖች የሚል ህግ ተረቅቆ ህዳር 30 ቀን 2005 ዓ.ም ለሲኖዶሱ ለውሳኔ እንዲቀርብ ተደርጎ በዚያው ሰሞን ምርጫው እንደሚከናወን የቤተ ክህነት ውስጥ አዋቂ ምንጮች አጋልጠዋል።

በቅርቡ ለፐትርክናው ይወዳደራሉ ተብሎ ከሚነገርላቸው ጳጳሳት መሀከል የአባ ጳውሎስ ደመኛ ጠላት ተደርገው የተፈረጁት አቡነ ሳሙዔል አንዱ ሲሆኑ እሳቸው በምርጫ ካሸነፉ አበቃልን እያሉ የአባ ጳውሎስ ደጋፊዎች ውስጥ ውስጡን እየተሩዋሩዋጡ መሆኑን ምንጮቹ አጋልጦዋል።

አባ ጳውሎስ በህይወት ሳሉ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የነበሩትን አቡነ ሳሙኤልን ስልጣን ለመከፋፈል እና ለመበታተን ሲሉ አዲስ አበባን በአራት ዞን እንዲከፋፈል እና አራት ጳጳሳት እንዲሾሙ ለሲኖዶሱ ጥያቄ አቅርበው የነበረ ቢሆንም ሲኖዶሱ በወቅት ሳያምንበት በመቅረቱ ሀሳቡ ውደቅ ተደርጎ የነበረ ሲሆን አሁን እሳቸው ከሞቱ በሁውላ ጥያቄው በድጋሚ ተነስቶ እንደጸደቀም ከምንጮቹ ለመረዳት ተችሎዋል።

በመጨረሻም ከመስከረም 27 ቀን 2005 ዓ.ም ጀምሮ ለወረዳ .....ለዞን.... ለክልል..... ብሎም ለዋናው መጅሊስ ተደረገ የተባለው የሙስሊሙ መሪዎች ምርጫ ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ.ም ተጠናቀቀ ተብሎ ቢነገርም ምርጫው ህጋዊ ውክልና ባለው አካል አልተደረገም በማለት ሙስሊሙ ህዝብ በተለያዩ ከተሞች ተቃውሞ ሲያስተጋባ ሰንብቶዋል።

ሙስሊሙ ህብረተሰብ ምርጫው ከመጀመሩ አስቀድሞ መፈትሄ አፈላላጊ ኮሚቲ መርጦ ቀጣይ ህጋዊ ምርጫ እንዲደረግ አሳስቦ የነበረ ቢሆንም ሀሳቡን በመቃወም እና በመጋፋት የኮሚቲ አባሎችን ለእስር ዳርጎ የወያኔ አባል የሆኑ ሰዎች እንዲቀመጡና ቦታውን እንዲቆጣጠሩ በመደረጉ ህዝቡ ቁጣውን ሰሞኑን ሲያስተጋባ መሰንበቱን ከተለያዩ ከተሞች የደረሰን ጥቆማ አጋልጦዋል።

የወያኔ  ደጋፊዎች የነጋዴ ፎረም አባል የሆነውንና የኦሮሚያ ክልል ተወላጁ  ሼህ ኪያር መሐመድ ኢማንን የመጅሊሱ ፕሬዝዳንት ከትግራይ ክልል የመጣውን ሼህ ከድር ማህሙድ አማን የተባለውን ግለሰብ ደግሞ ምክትል ፕሬዝዳንት አድርጎ የመረጠውን የማስመሰያ ምርጫ ሂደት ሙስሊሙ አጥንቆ እየተቃወመና እያወገዘ መሆኑን ከተለያዩ ከተሞቸ የደረሱን ጥቆማዎች አጋልጠዋል።

ሰኞ ዕለት ጥቅምት 26 ቀን 2005 ዓ.ም በሒልተን ሆቲል ተደረገ በተባለው የመጅሊስ ምርጫ የወያኔ ዋነኛ ሰዎች የሆኑትን አንዱን ከኦሮሚያ ሌላውን ከትግራይ ጠርተው ያስቀመጡት የወያኔ ቡድን መሪዎች ሙስሊሙ የመረጣቸውን መሪዎቹን በሽብርተኝነት ከስሶ ቃሊቲ እስር ቤት አጉሮዋቸው ከማሰቃየቱም ባሻገር ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንዳይገናኙ ማድረጉንም ከቤተሰቦቻቸው የደረሰን ጥቆማ አስረድቶዋል።

በምርጫው አሸነፉ የተባሉት የእስልምና ምክር ቤት አመራሮች ከዚህ በፊት ሙስሊሙ ተቃውሞ ሲያነሳ በግልጽም ሆነ በስውር የስለላ ስራ ሲሰሩና ለወያኔ ከፍተኛ የገንዘብ ድጋፍ ሲያደርጉ እንደነበር የጠቆሙት ቅርበት ያላቸው ወገኖች በተለይ በአዲሱ መጅሊስ ተመረጡ የተባሉት በዘር እና በብሔር....ላይ የተመረኮዘ በኮታ ተደልድለው የተቀመጡ መሆናቸውንም እነዚሁ ቅርበት ያላቸው ወገኖች አስረድተዋል።

ሙስሊሙ ህዝብ ምርጫው ተገቢና ፍትሀዊ ስላልሆነ አንቀበልም...... የታሰሩት መሪዎቻችን ይፈቱ...... ወያኔ ሙስሊሙን ንቆታል አላህ ይፋረደዋል .....በማለት በተለያዩ ከተሞች ተቃውሞውን እያስተጋባ እንደሚገኝ ከደረሰን ጥቆማ ለማወቅ ተችሎዋል።